ታህሳስ 23 ቀን 2016 ዓ/ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ለህገ መንግስት አጣሪ ጉባኤ

<u>አዲስ አበባ</u>

አቤቱታ አቅራቢ: ቅድሚያ ለሰብአዊ መብቶች ኢትዮጵያ (Human Rights First Ethiopia)

(በአዋጅ ቁጥር 1113/11 መሰረት በህግ ባለሙያዎችና ባለድርሻ አካላት ተመስርቶ በምዝገባ ቁጥር 4116 ተመዝግቦ ህጋዊ ሰውነት ያገኘ ሃገር በቀል የሲቪል ማህበር)

አድራሻ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 04 የቤት ቁጥር አዲስ

ተጠሪ: የትግራይ ክልል ግዚያዊ አስተዳደር

አድራሻ ትግራይ ክልል መቐለ ከተማ ሓወልቲ ክ/ከተማ

ጉዳዩ፣ <u>ከኢፌዲሪ ህገ መንግስት ዓንቀፅ 9 (1) የሚቃረን የትግራይ ክልል ጊዚያዊ አስተዳደር ያወጣው ደንብ ቁጥር 4/2016 እንዲሻር የህገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጠው ስለማመልከት</u>

ሀ) ማህበራችን በአዋጅ ቁጥር 798/2005 ዓንቀፅ 5 (3) መሰረት እና የማህበራችን መተዳደርያ ደንብ አንቀፅ 4(5) መሰረት ይህ አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው።

<u>የጉዳዩ መነሻ</u>

1) ከጥቅምት 24/2013 ዓ/ም ጀምሮ የትግራይ ሃይሎች በአንድ በኩል እንዲሁም የኢትዮጵያ ሃይሎችና አጋሮቻቸው መካከል የዘለቀው ጦርነት ጥቅምት 23/2015 ዓ/ም በአፍሪካ ህብረት አሸማጋይነት በፕሪቶርያ ደቡብ አፍሪካ ስምምነት የተደረገ መሆኑን ይታወቃል።

2) በስምምነቱ አንቀፅ 1(2) እና በተለያዩ ሌሎች አንቀፆች ሁሉም ሀይሎች ወደ ሕገ መንግስታዊ ስርአት እንዲመለሱ ተስማምተዋል።በትግራይ ክልል የተደረገ ምርጫ እና ምርጫውን ተከትሎ የቆመ ክልላዊ ምክር ቤት ሕገ መንግስታዊ አይደለም ተብሎ እንዲፈርስ መደረጉም ይታወቃል።

3) ሆኖም ግን የትግራይ ክልል ጊዚያዊ አስተዳደር የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት እና የትግራይ ክልል ሕገ መንግስት የሚቃረን አዲስ የመሸጋገርያ ደንብ ቁጥር 4/2016 የሚል ያወጣ በመሆኑ ደንቡ ሕገ መንግስታዊ አይደለም ተብሎ እንዲሻር የቀረበ አቤቱታ ነው።።

ዝርዝር አቤቱታ

1. ደንብ ቁጥር 4/2016 በፕሪቶርያ ስምምነት መሰረት ኢ-ሕገ መንግስታዊ ተብሎ የፈረሰው ምክር ቤት ያወጣቸው ሕጎች ተፈፃሚነታቸው እንዲቀጥል ያደረገ መሆኑን

1.1 ሕገ ወጥ ተብሎ በፈረሰው ምክር ቤት በ2014 ዓ/ም የትግራይ ክልል የፖሊስ ኮሚሽን ዳግም ለማቋቋም በሚል የወጣ አዋጅ ቁጥር 360/2014 ነባሩን የፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 221/2004 በመሻር የፖሊስ ኮሚሽኑን ሙሉ በሙሉ በማፍረስ እንደ አዲስ እንዲቋቋም አድርጓል። ይህ አዋጅ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ጦርነት ከመቀሰቀሱ በፊት በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ ፖሊስ ኮሚሽን ስር ሲሰሩ የነበሩ የፖሊስ አባላት ያለ ምንም ሕጋዊ ምክንያት ወደ ስራቸው እንዳይመለሱ እንደተደረጉ፣ ደመወዛቸውም እስከ ዛሬ ድረስ እንዳልተሰጣቸው እና ከነቤተሰቦቻቸው በከፍተኛ ስቃይ ውስጥ መሆናቸውን የጥሰቱ ተጠቂ ከሆኑ የትግራይ ፖሊስ አባላት ድርጅታችን ለማረጋገጥ ችሏል። ቁጥራቸው ከ1,000 በላይ የሚሆኑ እሰከ 30 ዓመት ያገለገሉ የትግራይ ክልል የፖሊስ አባላት ከስራቸው እንዲባረሩ ያደረገው ደግሞ ነባሩ የትግራይ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ፈርሶ የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን በአዋጅ ቁጥር 360/2014 እንደ አዲስ እንደተቋቋመ እና የሚመለመሉ የፖሊስ አባላትም ከትግራይ ሰራዊት ብቻ መሆኑ አዋጁ ስለሚያስገድድ ነው። የፕሪቶርያ ስምምነት ሁሉም ነገር ወደ ሕገ መንግስታዊ ስርዓት እንዲመለስና በሕገ መንግስቱ እና ሕገ መንግስቱን መሠረት በወጡ አዋጆችና በሌሎች ሕጎች ሁሉም እንዲመራ የሚያስገድድ ቢሆንም የትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር ግን ይህን ስምምነት በመጣስ በኢትዮጵያ እና በክልሉ ሕጎች መሠረት የተቀጠሩ፣ የሰለጠኑ እና ለዓመታት ያገለገሉ የፖሊስ አባላት "በትጥቅ ትግል አልተሳተፉም" በማለት ከስራ ማባረሩ ወይም ወደ ስራ እንዳይመለሱ መከልከሉ፣ እንደ ማንኛውም የፖሊስ አባላት የጥሮታ እና የሌሎች ማህበራዊ ዋስትና ጥበቃ እንዳያገኙ መከልከሉ ከስምምነቱ ውጭ የሆነ

ተግባር ከመሆኑም በላይ የአገራቱ ሕገ መንግስት፣ የክልሉ ሕገ መንግስት፣ ሌሎች መደበኛ ሕጎች እና አገሪቷ የተቀበለቻቸው አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችን እየጣሰ መሆኑ ያመላክታል። የፖሊስ አባላቱ ለማባረር ምክንያት የሆነው የክልሉ አዋጅ ቁጥር 360/2014 በጦርነቱ ወቅት በፕሪቶርያ ስምምነት መሰረት ሕገ መንግስታዊ አይደለም ተብሎ በፈረሰው የትግራይ ክልል ምክር ቤት የወጣ አዋጅ በመሆኑ፣ ሕገ መንግስታዊ አይደለም በተባለ ምክር ቤት የወጣ አዋጅ ደግሞ ሕጋዊ ሆኖ ተፈፃሚነቱ የሚቀጥልበት አግባብ የለም። የደንቡ የመሸጋገርያ ክፍል አንቀፅ 11 (2) ላይ "...አዋጅ ቁጥር 360/2014 ከመደበኛ ህጎች ጋር ተመዛዝኖ እስከሚሻሻል ድረስ ተፈፃሚነት ይኖረዋል..." በሚል በግልፅ ተፈፃሚነቱ እንደሚቀጥል ያመለክተ ስለሆነ የህገ መንግሰቱ ዓንቀፅ 9 (1) ማለትም **"ማንኛውም ህግ፣ ልማዳዊ አሰራር፣ እንዲሁም የመንግስት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ከዚህ ህገ መንግስት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም"** የሚል ድንጋጌ የሚቃረን ስለሆነ እንዲሻር እንጠይቃለን።

1.2 ኢ-ሕገ መንግስታዊ ተብሎ የፈረሰው ምክር ቤት 'የአስቸኳይ ጊዜ ሕጎች' በማለት በጦርነቱ ጊዜ የፌዴራሉ የወንጀል ሕግ የሚሸፍናቸውን ድንጋጌዎች ደግሞ በመዘርዘር ከባድ ቅጣት የሚያስከትሉ፣ የፌዴራሉ የወንጀል ሕግ ተፈፃሚነቱ እንዲቆም ያደረጉ ዝርዝር ድንጋጌዎች የያዙ አዋጆችና ደንቦች ኣውጥቶ ነበር። አሁን እንዲሻር የጠየቀንበት ደንብ ቁጥር 4/2016 አንቀፅ 9 (2) እና (3) ሕጎቹ በመሻር ከማረም ይልቅ የተከሰሱ ሰዎች ጉዳያቸው በነዚህ በጦርነቱ ወቅት የወጡ ሕጎች መታየቱ እንዲቀጥል አድርጓል። ይህ ድንጋጌ ሕገ ወጥ በተባለ ምክር ቤት የወጡ ሕጎች ተፈፃሚነታቸው እንዲቀጥሉ ከማድረጉ በተጨማሪ ከሕገ መንግስቱ አንቀፅ 55 (5) በፌዴራሉ ምክር ቤት የወጣ የወንጀል ሕግ ያልሸፈናቸው ካልሆኑ በስተቀር የወንጀል ሕግ በፌዴራል ምክር ቤት ይወጣል የሚል የህገ መንግስት ድንጋጌ የሚቃረን ነው። በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወጡ የተባሉ የወንጀል ሕጎች የፌዴራሉ የወንጀል ሕግ የደነገጋቸው በመድገም የወጡ ነበሩ። ስለዚህ ደንቡ ከሕገ መንግስቱ አንቀፅ 9(4) እና 55 (5) የሚቃረን በመሆኑ ሊሻር ይገባል።

2. **ደንቡ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግሰት ዓንቀፅ 37 ፣ አንቀፅ 80 (3) (ሀ) እና አንቀፅ 9(4) የሚቃረን መሆኑን**

2.1 የደንቡ አንቀፅ 10 (2) በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት በአስቸኳይ ጊዜ አዋጆች ዕልባት ያገኙ የወንጀል እና የፍትሐብሄር ጉዳዮች ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይግባኝ እንዳይባልበት ታግዶ ይቆያል በማለት ደንግጎ ይገኛል፡፡ ይህ ደግሞ የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 80 (3) (ሀ)

“የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን ይኖረዋል” የሚለውን ድንጋጌ በግልፅ የሚቃረን ነው፡፡ ስለሆነም ደንቡ ከሕገ መንግስት የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 9(4) መሠረት ውድቅ እንዲደረግ እንጠይቃለን፡፡

2.2 የደንቡ የመሸጋገርያ ክፍል ዓንቀፅ 11 (3) በግልፅ ከጥቅምት 24/ 2013 ዓ/ም እስከ ህዳር 30/ 2015 ዓ/ም ያለው ጊዜ የመንግስት ሰራተኛ፣ የግል ተቋማት ሰራተኛና የግለሰብ ሰራተኛ ውዝፍ ደመወዝ የሚመለከት አዲስ ክስ ጉዳይ ታግዶ ይቆያል በማለት ደንግጎ ይገኛል፡፡ በተመሳሳይ በሂደት ላይ ያሉ የክስ፣ ይግባኝና የአፈፃፀም ጉዳዮች በሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ተጠንቶ መፍትሄ እስከሚደረግበት ባለበት ይቆያል በማለት ደንግገዋል፡፡ በመሆኑም የደንቡ ዓንቀፅ 11 (3) በግልፅ የዜጎች ህገ መንግስታዊ መብት የሆነው በሕገ መንግሰቱ ዓንቀፅ 37 (1) የተደነገገው ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው የሚል መብት ገደብ ያስቀመጠ ነው፡፡ ስለሆነም ስልጣን ባልተሰጠው አካል ለዛውም በደንብ ዜጎች ያላቸው የፍትህ ጥያቄዎች መከልከል ዜጎች መብታቸውን በፍርድ ቤት ወይም ሌሎች የዳኝነት አካላት እየቀረቡ መብታቸው ለማስከበር ያላቸው መብት የሚገድብ ነው፡፡ዜጎች በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ካላቸው ለፍርድ ቤት በማቅረብ እንደ የጉዳዩ እየታየ መወሰን ሲገባው ገና ለገና ጉዳዮች በፍርድ ቤት እንዳይታዩ ለመከልከል የተደረገው የህግ ክልከላ ተገቢነት የሌለውና ህገ መንግስቱን የሚጥስ ስለሆነ ሊሻር የሚገባው ነው፡፡

ከህግ መንግስት አጣሪ ጉባኤ የምንጠይቀው ዳኝነት

ከላይ በዝርዝር እንዳቀረብነው በትግራይ ግዚያዊ አስተዳደር ከህዳር 28/03/2016 ዓ/ም ጀምሮ ተፈፃሚ እንዲሆን የወጣው ደንብ ቁጥር 4/2016 የህገ መንግሰቱን ዓንቀፅ 9 (1) ፣

አንቀፅ 37 ፣ አንቀፅ 55 (5) እንዲሁም አንቀፅ 80 (3)ሀ) የሚቃረን ስለሆነ የህገ መንግስት ትርጉም ስለሚያስፈልገው ወደ ፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲላክ እንዲደረግ እናመለክታለን፡፡

<u>የማስረጃ ዝርዝር</u>

ሀ) የሰው

1) ረዳት ፕሮፌሰር ሙሴ መዝገቦ ገብረመድህን አድራሻ አዲስ አበባ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 9 (የደንቡ ኢ-ህገ መንግስታዊነት በተመለከተ ማብራርያ የሚሰጡ የህግ ባለሙያ)

ለ) የሰነድ

1) የትግራይ ጊዚያዊ መንግስት ያወጣው ደንብ ቁጥር 4/2016 13 ገፅ

2) ቅድሚያ ለሰብአዊ መብቶች ኢትዮጵያ (Human Rights Firs- Ethiopia) በአዋጅ ቁጥር 1113/11 መሰረት በህግ ባለሙያዎችና ባለድርሻ አካላት ተመስርቶ በምዝገባ ቁጥር 4116 ተመዝግቦ ህጋዊ ሰውነት ያገኘ ሃገር በቀል የሲቪል ማህበር ስለመሆኑ የሚያሳይ ፈቃድ 01 ገፅ

3) ቅድሚያ ለሰብአዊ መብቶች ኢትዮጵያ (Human Rights First Ethiopia) ተጠቃሹ ደንብ የክልሉ ጊዚያዊ አስተዳደር እንዲያርመው የፃፈው ደብዳቤ እና ያወጣው መግለጫ ~~09~~ ገፅ

ያቀረብነው አቤቱታ እውነት መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡